በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-198891

ቀን፡-02/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ አክሉሉ ካሕሳይ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አኪር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር - በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ጥር 25 ቀን 2005 ዓ/ም በተደረገ የመኪና ኪራይ ውል ስምምነት መሠረት የሠሌዳ ቁጥር 3-83597 አ.አ. የሆነ ተሽከርካሪ ለ10 ወራት ከ15 ቀናት ለሰራው ብር 346,500.00 ተጠሪ መክፈል ሲገባው ብር 100,000.00 ብቻ ከፍሎ ቀሪ ገንዘብ ስላልከፈለ ብር 246,500.00 ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረበው መልስ የሠዓት መቆጣጠሪያ ሳያቀርቡ ብር 136,147.00 ከፍለናል፡፡ በውሉ መሠረት ታይምሽት ሳይቀርቡ ክፍያ መጠየቃቸው አግባብነት የለውም፡፡ የቀረበው ማስረጃም በአመልካች መኪና ሥራ መስራታችን አያሳይም፤ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራቀኙን ማስረጃ በመስማት በውሉ መሠረት የተሰራውን ስራ በሠዓት መቆጣጠሪያ ማስረዳት አለበት፡፡ በአመልካች የቀረበው የሠዓት መቆጣጠሪያ ለክሱ መነሻ በሆነው መኪና የተሰራ ስራ ስለመኖሩ አያስረዳም፡፡ የቀረቡት ምስክሮችም መኪናው መከራየቱን እንጂ ስለክፍያው የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ከብር 100,000.00 በላይ መክፈሉን አስረድቷል፡፡ ቀሪ ክፍያ ያለበት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፤ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ይዘትም በግራቀኛችን የተደረገው ውል እና የቀረበው የሠዓት መቆጣጠሪያ ክፍያው ብር 346,500.00 መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ መክፈሉን ማስረዳት ያለበት ተጠሪ ነው፤ ብር 346,500.00 መክፈሉን አላስረዳም፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የሠዓት መቆጣጠሪያ ቀርቦ እያለ በሥር ፍርድ ፍርድ ቤት አልቀረበም ተብሎ ክሱ ውደቅ መደረጉ ተገቢነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ ተጠርቶ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት የያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ጥር 25 ቀን 2005 ዓ/ም በተደረገ የመኪና ኪራይ ውል ስምምነት መሠረት የሠሌዳ ቁጥር 3-83597 አ.አ. የሆነ ተሽከርካሪ ለ10 ወራት ከ15 ቀናት ለሰራው ተጠሪ መክፈል ሲገባው ያልከፈለው ቀሪ ገንዘብ ብር 246,500.00 ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የሚከራከረው በውሉ መሠረት የሠዓት መቆጣጠሪያ ሳያቀርቡ ክፍያ መጠየቃቸው አግባብነት የለውም፡፡ የቀረበው ማስረጃም በአመልካች መኪና ሥራ መስራታችን አያሳይም፤ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ነው፡፡ ግራቀኙ ባላቸው የመኪና ኪራይ ውሉ ስምምነት መነሻ ያደረገ ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡትን ክስ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ወስነዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሥር ፍርድ ቤት ሆነ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በሕግ ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ናቸው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ ነገር ግን ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም (burden of production) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ፣ በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፣ የተለየ የማስረዳት ደረጃ (standard of proof) የሚጠይቁ ጉዳዮችን በሚጠይቀው ደረጃ ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ

የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎምና አተገባበር ስህተትና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ይሆናል፡፡

በያዘነው ጉዳይ የግራቀኙ የመኪና ኪራይ ውል አንቀጽ 9 እና 10 መሠረት የሠዓት መቆጣጠሪያ ማስረጃ በአከራይ እና ተከራይ ተወካይ ተሞልቶ በፕሮጀክቱ ኃላፊ ተረጋግጦና ፀድቆ ለክፍያ መቅረብ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ አመልካችም በሥር ፍርድ ቤት የሰዓት መቆጣጠሪያ ሠነድ እና የሠው ማስረጃዎች አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ማስረጃውን የመዘነ ሲሆን የሠዓት መቆጣጠሪያ ሠነድ መቅረቡን ገልጾ ነገር ግን ሠነዱ አመልካች ክስ ያቀረቡበት የሠሌዳ ቁጥር 3-83597 አ.አ. የሆነ ተሽከርካሪ የሚመለከት አይደለም፣ የሠው ምስክሮችም ስለክፍያው መጠን አያውቁም በሚል ውድቅ ያደረገው ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ይህም ውሳኔ ላይ የተፈጸመ የማስረጃ አቀባበል ሆነ ምዘና መርሕ ስህተት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው መክፈሉን ማስረዳት ያለበት ተጠሪ ነው ያሉ ቢሆንም አመልካች በውሉ የተመለከተው መኪና ምን ያህል ሰዓት እንደሰራ ባላስረዱበት ሁኔታ የማስረዳት ግዴታው ወደተጠሪ የሚዞርበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 256601 ጥቅምት 12 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 83281 የካቲት 16 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡